# ባጭር ፡ ቃል ፡ ሰፊ ፡ ሐሳብ ።

መርዝም ፡ መድኀኒት ፡ ነው ፡ ሲሆን ፡ በጠብታ ፡
እንዲሁም ፡ ለተንከል ፡ አለው ፡ ቦታ ፡ ቦታ ፡

ምን ፡ ቢሠለጥኑ ፡ ቢራቀቁ ፡ በጣም ፡
ሁል፡ጊዜ ፡ ደጋግሞ ፡ ብልጠት ፡ አያዋጣም ፡

በእጅ ፡ የተበተቡት ፡ ተንኰል ፡ ዞሮ ፡ ዞሮ ፡
ማጋለጡ ፡ አይቀርም ፡ እጅና ፡ እግር ፡ አስሮ ።

መጽሐፉም ፡ ይለናል ፡ ሲያስተምር ፡ ጥበብ ፡
ብልጥ ፡ ሁን ፡ እንደ ፡ እባብ ፡ የዋህ ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡
ስለዚህ ፡ በብልጠት ፡ ተንኮል ፡ ስትሠሩ ፡
በዝቶ ፡ እንዳይገድላችሁ ፡ ገርነት ፡ ጨምሩ ።

ሁለት ፡ ባልንጀሮች ፡ በጣም ፡ ሲዋደዱ ፡
አንደኛው ፡ በሐሰት ፡ አንደኛው ፡ ከሆዱ ፡
ወስላታው ፡ በሥራው ፡ ሲጠፋ ፡ እየከዳ ፡
ሐቀኛው ፡ ግን ፡ ተርፎ ፡ ሁሉንም ፡ ሲረዳ ፡
ደግና ፡ ክፉን ፡ ሰው ፡ እግዜር ፡ እየለየ ፡
ፍርዱን ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ይባላል ፡ አሳየ ።

የቅናት ፡ በሽታ ፡ ሕመሙ ፡ የከፋ ፡
የሕሊናን ፡ ዐይኖች ፡ ጨርሶ ፡ እሚያጠፋ ፡
በዚህ ፡ ክፉ ፡ ደዌ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሲለከፍ ፡
የተጣራው ፡ ነገር ፡ ይመስለዋል ፡ ሰፈፍ ፡
ልቡም ፡ እያዳላ ፡ ወደ ፡ ክፋት ፡ ወገን ፡
መሞትን ፡ ይመርጣል ፡ ሰውን ፡ ከማመስገን ።

ሕይወት ፡ ጦርነት ፡ ነው ፡ ዋጋህን ፡ የሚያሳይ ፡
መታገል ፡ ግድ ፡ ነው ፡ ስትኖር ፡ ባለም ፡ ላይ ፡
በገዛ ፡ እጁ ፡ ወድቆ ፡ በቁሙ ፡ እየሞተ ፡
መታገል ፡ ያልቻለ ፡ ልቡ ፡ እየታከተ ፡
የሚያነሣው ፡ የለም ፡ በፍቅር ፡ በእርዳታ ፡
በዚች ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ፍጡር ፡ ካልበረታ ፡
ጥንቱን ፡ አልተሠራም ፡ ለስንፎች ፡ ቦታ ።
ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ የየስዉን ፡ ዋጋ ፡
መሆን ፡ ያስፈልጋል ፡ አእምሮው ፡ የረጋ ፡
ባስተዋይነትም ፡ መሆን ፡ ባለጸጋ ።

ሁሉን ፡ በማሻሻል ፡ መጨመር ፡ መቀነስ ፡
የሌለውን ፡ መፍጠር ፡ ያለውንም ፡ ማደስ ፡
መልካሙን ፡ አስፋፍቶ ፡ መጥፎውን ፡ መደምሰስ ፡
የሚጓዝበትን ፡ ዐቅድ ፡ እያሠመሩ ፡
ከጨለማ ፡ አውጥቶ ፡ ሕዝብን ፡ እየጠሩ ፡
አሳብ ፡ እያቀዱ ፡ ሠርቶ ፡ በማሠራት ፡
ግንባር ፡ ቀደም ፡ ሆኖ ፡ ያስፈልጋል ፡ መምራት ።
የተማረ ፡ ሆኖ ፡ ዕውቀት ፡ እያበራ ፡
የቀሩትን ፡ ሰዎች ፡ በጥበብ ፡ ካልመራ ፡
ጥቅም ፡ የሌለው ፡ ነው ፡ ድካሙ ፡ ከሣራ ።

ፍጥረት ፡ ደስ ፡ ሲለው ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ተክዝ ፡
ሌሎቹ ፡ ሲመኩ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ፍዘዝ ፡
አምረው ፡ ሲጊያጊያጡ ፡ መናኛውን ፡ መልበስ ፡
እንዲሁም ፡ ይሻላል ፡ ሲሣሣቁ ፡ ማልቀስ ፡
ሌላው ፡ ሲጠቃቀም ፡ ሌላው ፡ ሲረዳዳ ፡
ላንተ ፡ ይበጅሃል ፡ ዐውቀህ ፡ ብትጎዳ ፡
ቀኙ ፡ ግራ ፡ ሆኖ ፡ ፍጡር ፡ ሲደናበር ፡
ማለት ፡ ትችላለህ ፡ እኔ ፡ ዐውቄው ፡ ነበር ።
ብርሃንና ፡ ጽልመት ፡ መሬትና ፡ ባሕር ፡
ተራራና ፡ ሜዳ ፡ ጠፈርና ፡ ምድር ፡

ሰዎችና ፡ አራዊት ፡ ጠጠርና ፡ ኮከብ ፡
ውበትና ፡ ጭቃ ፡ ጉድለትና ፡ ጥበብ ፡

አብረው ፡ ተቀላቅለው ፡ ሆነው ፡ ትልቅ ፡ መዓት ፡
ሥራት ፡ የሚያጡበት ፡ የብጥብጥ ፡ ሰዓት ፡

መኖሩን ፡ ካመነ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በከንቱ ፡
ሥራት ፡ ልሥራ ፡ ብሎ ፡ ባለም ፡ ላይ ፡ መልፋቱ ፡
ያስደንቃል ፡ በጣም ፡ አወይ ፡ ሞኝነቱ ።

አንድ ፡ አዲስ ፡ ተገኝቶ ፡ ሌላው ፡ ግን ፡ ካረጀ ፡
የሚናደው ፡ ነገር ፡ ላዲሱ ፡ ከበጀ ፡
በዘመን ፡ መለወጥ ፡ እየተነወረ ፡
ይቅር ፡ ከተባለ ፡ ልማድ ፡ የነበረ ፡
ጠቃሚ ፡ ከሆነ ፡ ሲነቀል ፡ ሲጠፋ ፡
ማፍረስም ፡ መሥራት ፡ ነው ፡ ይለናል ፡ ፈላስፋ ።

ዐይን ፡ የለውም ፡ አሉ ፡ የሰነፍ ፡ ልመና ፡
ወደ ፡ አምላክ ፡ ሲጸልይ ፡ ማታ ፡ በልቡና ፡

መንገዱ ፡ ሳይመታኝ ፡ ባቡዋራ ፡ በጭቃ ፡
አድርገኝ ፡ ይለዋል ፡ ላገሬ ፡ እንድበቃ ፡
እንጠጠ ፡ ተኝቼ ፡ አሥመራ ፡ እንድነቃ ።
እየተሻሻለ ፡ እየተለወጠ ፡
አንደኛው ፡ ከሌላው ፡ አምሮ ፡ እየበለጠ ፡
ሁል ፡ ጊዜ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ሠርቶ ፡ በመሰብሰብ ፡
በኑሮ ፡ በሥራ ፡ በልማድ ፡ በጥበብ ፡
ካልተፈራረቁ ፡ ለቅሶና ፡ ደስታ ፡
ትካዜና ፡ ዘፈን ፡ ሣቅና ፡ ጨዋታ ፡
ቀይና ፡ አረንጓዴ ፡ ጥቍርና ፡ ብጫ ፡
ኑሮዋችን ፡ ጣዕም ፡ ያጣ ፡ ይሆናል ፡ አልጫ ።

ዓለምን ፡ ካልናቀ ፡ ሰው ፡ መልካም ፡ አይሠራም ፤
ሞቱን ፡ ካላሰበ ፡ አምላኩን ፡ አይፈራም ፡
ሲቀር ፡ እያየነው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ሞቶ ፡
ልባችን ፡ በኀዘን ፡ ይኑር ፡ ተኮራምቶ ፡
ዘወትር ፤ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ባንዳንዱ ፡ ደቂቃ ፡
ይህንን ፡ ሊያስታውስ ፡ መንፈሳችን ፡ ይንቃ ፡
ሁብቱም ፡ ሰውነቱም ፡ አፈር ፡ ውስጥ ፡ ሲገቡ ፡
መሬት ፡ የማይበላው ፡ የማይሞት ፡ ጥበቡ ፡
እውነተኛነቱ ፡ ነው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ገንዘቡ ።

www.ethiopianorthodox.org

ሰው ፡ ሲበድላችሁ ፡ እስቲ ፡ አትናደዱ ፡
ጠላትን ፡ አትጥሉ ፡ ክፉን ፡ ሰው ፡ ውደዱ ፡
የክፉ ፡ ሰው ፡ ክፋት ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ፡ ትርፉ ፡
ያነቃቃችኋል ፡ እንዳታንቀላፉ ።
የልቡናው ፡ ስሜት ፡ እየተራቀቀ ፡
ሁል ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ በጣም ፡ እየላቀ ፡
በሥራ ፡ በጥበብ ፡ ግሎ ፡ ለመነሣት ፡
ቈስቋሽ ፡ ይፈልጋል ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ እሳት ።

ሀብታም ፡ ይደኸያል ፡ ሐኪምም ፡ ይሞታል ፤
ጕበዝ ፡ ይሸነፋል ፡ ብልኅ ፡ ይሳሳታል ፤
የበራውም ፡ ጠፍቶ ፡ የሠሩት ፡ ይፈርሳል ፤
የቆመውም ፡ ወድቆ ፡ የሣቀ ፡ ያለቅሳል ፡
ጌጥም ፡ ሆነ ፡ ጥበብ ፡ ውበት ፡ ሆነ ፡ ክብርም ፤
ያማረበት ፡ ነገር ፡ ማስቀየሙ ፡ አይቀርም ።

ፍሬ ፡ መሬት ፡ ወድቆ ፡ ከዋለ ፡ ካደረ ፡
ሰው ፡ ገንዘብ ፡ አግኝቶ ፡ መክበር ፡ ከጀመረ ፡
የመጣ ፡ ነውና ፡ ቀድሞውን ፡ ከጥንት ፤
ሁለቱም ፡ አይድኑ ፡ ከመበላሸት ።

የሰዎችን ፡ ጠባይ ፡ የተመራመረ ፡
ብልኁ ፡ ፈላስፋ ፡ እንዲህ ፡ ተናገረ ፡
በጣም ፡ በማስተዋል ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፤
ስመለከታቸው ፡ የሰውን ፡ ልጆች ፡
እያጣሁባቸው ፡ ግብሩ ፡ እሚመሰገን ።
እንቃቸው ፡ ጀመር ፡ እጅግ ፡ አለመጠን ።

የደንቆሮ ፡ መንፈስ ፡ ምንኛ ፡ ታደለ ።
ብልጥነት ፡ አላጣም ፡ ጅል ፡ እየመሰለ ፡
እንኳን ፡ መጽሐፍ ፡ ማንበብ ፡ ፊደል ፡ ሳያጠና ፤
ሁሉንም ፡ ያወቀ ፡ ይመስለዋልና ።

የሊቅ ፡ ሰው ፡ መከራ ፡ የብልኅ ፡ አባዜ ፤
ሲጨነቅ ፡ መኖር ፡ ነው ፡ ባሳብ ፡ በትካዜ ፡
አቶ ፡ ዐሳበ ፡ ቢስ ፡ ይተኛል ፡ ዝም ፡ ብሎ ፤
ከትራሱ ፡ ጋራ ፡ ዐሳቡን ፡ ጠቅሎ ።

ኵራትና ፡ ትዕቢት ፡ የሞሉት ፡ እናት ፤
ሰይፍና ፡ ጕራዴ ፡ የመቱት ፡ አንገት ፡
አይገላገሉም ፡ እንዲህ ፡ በቀላሉ ፡
እመሬት ፡ ላይ ፡ ወድቀው ፡ ሳይንከባለሉ ።

ገንዘብ ፡ መፈጠሩ ፡ ለሰው ፡ አገልጋይ ፤
ሆኖ ፡ ሊሠራበት ፡ አልነበረም ፡ ወይ ?
አሁን ፡ ግን ፡ መስገብገብ ፡ በጣም ፡ ስለ ፡ በዛ ፤
ሰው ፡ ባሪያ ፡ እየሆነ ፡ ለገንዘብ ፡ ተገዛ ።

የሐሰት ፡ ወገኖች ፡ ተመችን ፡ እያሉ ፡
ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አድመው ፡ እየተማማሉ ፡
እውነትን ፡ ካለም ፡ ላይ ፡ ሊያጠፉዋት ፡ ተነሡ ፡
እውነት ፡ ግን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ መከታ ፡ ለነሱ ፡
ታግሳ ፡ እያሸነፈች ፡ ስትኖር ፡ ረግታ ፤
ጠላቶችዋ ፡ ሁሉ ፡ በሱዋ ፡ ጥፋት ፡ ፈንታ ፡
አንድ ፡ ባንድ ፡ ወድቀው ፡ እየተሰበሩ ፤
ከስማቸው ፡ ጋራ ፡ ሁሉም ፡ ጠጥፍተው ፡ ቀሩ ።

ባለም ፡ ላይ ፡ ተሠርቶ ፡ በብዙ ፡ ጥበብ ፤
ማዕርግ ፡ የሚባለው ፡ የደረጃ ፡ ግንብ ፡
በዚህ ፡ በሚያዳግት ፡ ባቀበት ፡ መንገድ ፡
ግማሹ ፡ ሲወጣ ፡ ግማሹ ፡ ሲወርድ ፡
ከወደ ፡ ዳር ፡ ቆሞ ፡ ማስተዋሉን ፡ ሳይተው ፤
ምንኛ ፡ ደስ ፡ ይላል ፡ ለተመለከተው ።

ብልኅ ፡ አስተዋይ ፡ ሰው ፡ ያለምን ፡ ነገር ፤
ዘልቆና ፡ ጠንቅቆ ፡ የሚመራመር ፤
ትልቅ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ረቂቅ ፡ ምስጢር ፡
ብለው ፡ በሹልክታ ፡ አድርገው ፡ ሽፍን ፤
የዚህ ፡ ዓለም ፡ ሰዎች ፡ የሚያወሩትን ፤
በተረዳው ፡ ጊዜ ፡ መርምሮ ፡ እያጣራ ፤
በመገረም ፡ ብዛት ፡ ሥቆም ፡ አያባራ ።

ሰው ፡ ከሚሉት ፡ ከንቱ ፡ የማይለወጥ ፤
ኧረ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ የማይገለጥ ፤
ምን ፡ ምስጢር ፡ ይገኛል ፡ በዚች ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ?
የሥጋና ፡ የነፍስ ፡ የዕድሜንም ፡ ነገር ፤
የመወለድና ፡ የሞትን ፡ ምስጢር ፡
መርምሮ ፡ ሊያስረዳ ፡ ስንት ፡ ሊቅ ፡ ተመኘ ፤
ግን ፡ ሁሉም ፡ በከንቱ ፡ ባሳብ ፡ ባሕር ፡ ዋኘ ፤
ሰው ፡ እንቆቅልሽ ፡ ነው ፡ ፍቺው ፡ ያልተገኘ ።

ደስታ ፡ ጭቃ ፡ ነው ፡ ነፍስን ፡ ያሳድፋል ፤
ታድላ ፡ ጭቅቅት ፡ ነው ፡ ጠባይን ፡ ያጠፋል ፡
እንዶዱ ፡ ኅዘን ፡ ነው ፡ ውኃውም ፡ መከራ ፤
ጠበሉም ፡ ዐሳር ፡ ነው ፡ ነፍስን ፡ የሚያጠራ ።
እጅግ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ ባየህ ፡ ጊዜ ፡
ደስታህን ፡ ትተህ ፡ ዙር ፡ ወደ ፡ ትካዜ ፡
በዚህ ፡ ደስታ ፡ ውስጥ ፡ ላይን ፡ የተሰወረ ፡
ያንኑ ፡ የሚያህል ፡ በጣም ፡ የመረረ ፡
ሽክሙ ፡ የከበደ ፡ ወዮታው ፡ የጠና ፡
አንድ ፡ ትልቅ ፡ ኅዘን ፡ አይታጣምና ።

ከከበደ ፡ ሚካኤል ።

የቅኔ ፡ አዝመራ ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፺፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ።

www.ethiopianorthodox.org